በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ፍትህ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር የሕ/ም/ማጠ/ዳ/1463/18
ቀን 21/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገንዘብ ቢሮ
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

የአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 (ሀምሌ 2018 ዓ.ም የተሻሻለ) ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን ለፍትህ ቢሮው በመላክ ማስመዝገብ እንዳለበት ደንግጓል።

በዚህ መሰረት ገንዘብ ቢሮ በቁጥር አብክመ/ገቢ/20 በቀን 04/12/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር. 10/2013" እንዲመዘገብ መላኩ ይታወሳል። ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ መመሪያው በክልል ደረጃ ቁጥር ተሰጥቶ መመሪያ ቁጥር 155/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲዉል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ በተቋማችሁ ድረ ገጽ ጭናችሁ ተግባራዊ ማድረግ የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን የተመዘገበዉን መመሪያ ቅጅ 06 ገጽ በሀርድና ሶፍት ኮፒ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

'ከሰላምታ ጋር'

ሺድጋፍ ኃይሌ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል
ዳይሬክቶሬት የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ

ቁጥር 155/2018



መስከረም / 2013 ዓ/ም

ባህር ዳር

መመሪያ ቁጥር. 155/2018

የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ

በክልሉ የሚወሰኑ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህ መመሪያ አውጥቷል::

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር. 155/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ወይም በገቢ ግብር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል:: ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም:-

1/ **"የታክስ ጊዜ"** ማለት ከታክስ ጋር በተያያዘ ለገቢዎች ቢሮ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ታክስ የሚሸፍነው ጊዜ ነው::

2/ **"ያልተከፈለ ታክስ"** ማለት በመክፈያ ቀን ወይም ገቢዎች ቢሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ቀን ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ታክስ ነው::

3/ **"ቢሮ "** ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ማለት ነው::

4/ **"የገቢዎች ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ መምሪያዎችን፣ጽ/ቤቶች እና የቀበሌ ማእከላትን ይጨምራል::

5/ **"አዋጅ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው:

6/ **"ደንብ"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2010 ነው::

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 መሰረት በሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

ክፍል ሁለት

የአስተዳደራዊ ቅጣቶች አወሳሰን

4. ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች

1/ ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በሕግ የመመዝገብ ግዴታ ላለባቸው እንዲሁም ሥራቸውን ሲያቆሙ ምዝገባው እንዲሠረዝ የማድረግ ግዴታ ለተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ነው::

2/ ለአዋጁ አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 4 አፈጻጸም በቂ ምክንያት ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ካቆመ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰቱ አደጋዎች ያጋጠመው እንደሆነ፣ ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴው በጽኑ ህመም ላይ የሚገኝ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ እንደሆነ ነው::

5. ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት

1/ ለአዋጁ አንቀጽ 101 አፈጻጸም በታክስ ህጉ መሠረት መያዝ የነበረበት ሰነድ ማለት-

ሀ. የገቢ ግብርን በሚመለከት ለደረጃ ሀ የትርፍና ኪሳራ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ ለደረጃ ለ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም እነዚህን መግለጫዎች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑ ሰነዶች

ለ. የተጨማሪ እሴት ታክስና ተርን አቨር ታክስ በሚመለከት የግዥና ሽያጭ መዝገብና ታክሱን ለማስላት የሚረዱ ደጋፊ ሰነዶች፣

ሐ. የኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት ታክሱን ለማስላት የሚያግዙ የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች፣

2/ ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንደያዘ የሚቆጠረው ያቀረበው ሰነድ ስለመዝገብ አያያዝ ገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መቅረብ የቀረበ እና አስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች እንዲያቀርብ ገቢዎች ቢሮ ሲጠይቀው ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው::

3/ ለአዋጁ አንቀጽ 101 ንኡስ አንቀጽ 2 (ሀ) እና (ለ) አፈጻጸም የታክስ ዘመን ማለት:-

ሀ. ለገቢ ግብር ማስታወቂያ የሚቀርብበት ታክስ የሚሸፍነው የአንድ ዓመት ጊዜ፣

ለ. ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንደ ታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን አንድ ወር ወይም ሶስት ወር፣

ሐ. ለተርን አቨር ታክስ የደረጃ ሀ ታክስ ከፋዮች አንድ ወር ፣ ለደረጃ ለ ታክስ ከፋዮች ሶስት ወር

ነው።።

መ. ለኤክሳይዝ ታክስ ምርት አንድ ወር ነው።።

6. ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት

ለአዋጁ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 3 አፈጻጸም "የገንዘብ ጥቅም " ማለት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው የራሱ ያልሆነውን መለያ ቁጥር በመጠቀም በሰራው ስራ ካገኘው የሽያጭ ገቢ ገቢውን ለማግኘት ያወጣው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ ያለው ልዩነት ነው።።

7. የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት

1/ የታክስ ማስታወቂን ዘግይቶ በማቅረብ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 35 መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ሊቀርብላቸው በሚገባ፡-

ሀ. በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ መሰረት መቅረብ በሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፣

ለ. በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ መሰረት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ታክስ በሚመለከት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ሐ. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት የሚቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ፣

መ. ወደ አገር በገባ ዕቃ ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣

ሠ. በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ረ. በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሰረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ እና

ሰ. በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት በታክስ ከፋዩ መቅረብ የነበረበት የታክስ ማስታወቂያ ላይ ነው።።"

2/ የአዋጁ አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ 1 ለተጣለው ቅጣት "የታክስ ጊዜ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 38 በተሰጠው ትርጉም መሰረት ሆኖ የቅጣት አወሳሰኑ፡-

ሀ. ለገቢ ግብር አዋጅ በአመት፣

ለ. ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንደ ታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን በየወሩ ወይም በየሶስት ወሩ፣

ሐ. የደረጃ ሀ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ለእያንዳንዱ በወር

መ. ለኤክሳይዝ ታክስ በወር ፣

ሠ. ለደረጃ ለ ለተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ በየሶስት ወሩ፣

ረ. ከተከፋይ ሂሳብ ተቀንሶ የተከፈለን ሳይጨምር የሰንጠረዥ መ ገቢ በአዋጁ አንቀጽ 103 መሠረት የሚሰላ ይሆናል።።

3/ በአዋጁ አንቀጽ 103 መሠረት የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው የዘገየው የታክስ ማስታወቂያ እንደ አንድ ጥፋት ተቆጥሮ አንድ ቅጣት ተግባራዊ በማድረግ ነው።።

4/ ይህ አንቀጽ በደረጃ ሐ ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።።

8. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት

1/ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ባለመክፈል በአዋጁ አንቀጽ 105 ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የሚጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የቀረው ገንዘብ በታክስ መክፈያ ጊዜ ባለመክፈሉ ይሆናል።

2/ በአዋጁ አንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት ግብር ቀንሶ ገቢ የላደረገ፡-

ሀ. የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ፣ እና

ለ. ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ዋና ሂሳብ ሹም የሌለ እንደሆነ ታክስ ቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መክፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ በአያንዳንዱ የታክስ መክፈያ ጊዜ ተቀንሶ ገቢ ላልተደረገ ግብር እያነዳንዳቸው ብር 2000 ቅጣት ይከፍላሉ።

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ቢኖርም አንድ ሰው ከአንድ በላይ ኃላፊነቶች ደርቦ የሚሰራ ከሆነ የሚጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው እንደ አንድ ኃላፊ ብቻ ይሆናል።

4/ በአዋጁ አንቀጽ 105 ንኡስ አንቀጽ 3 የሚጣል ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92/3/ ተፈጻሚ በሚደረግባቸው ገቹ እና አቅራቢ ላይ ነው።

9. ደረሰኝ ባለመስጠት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ደረሰኝ በመስጠት የሚጣል ቅጣት

1/ በአዋጁ አንቀጽ 107 መሠረት ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥው ባልሰጠው ለእያንዳንዱ ግብይት ብር 50000 ይቀጣል። ይህ ድንጋጌ ማንዋል ደረሰኝ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ የሆነ ታክስ ከፋይ ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለሚቀነስ ግብር ለሚሰጥ ደረሰኝን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

10. ታክስ አሳንሶ በማስታወቅ የሚጣል ቅጣት

በአዋጁ አንቀጽ 108 መሰረት የተጣለው ቅጣት ጥፋቱ መጀመሪያ ጊዜ፣ ለሁለተኛ ጊዜ፣ ለሶስተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ የተፈጸመ በሚሆንበት ጊዜ የተለያየ ሲሆን የጥፋቱ መጠን የሚቆጠረው አዋጁ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለየታክስ ዓይነቱ ተለያይቶ እና የታክስ ስሌት ውሳኔው በአንድ ጊዜ የተወሰነ ቢሆንም ጥፋት በተገኘባቸው የታክስ ማስታወቂያዎች ብዛት ነው።

11. ታክስን በመሸሽ የሚጣል ቅጣት

በአንቀጽ 109 የተጣለው ቅጣት በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 75 እስከ 78 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 60 ታክስን መሸሽ ለመከላከል የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በመተላለፉ በተፈጸሙ ድርጊቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

12. የታክስ ማስታወቂያ እና መክፈያ ጊዜ

1/ አንድ ታክስ ከፋይ ታክስ ያስታወቀበት እና የከፈለበት ጊዜ የተለያየ ከሆነ ታክስ ባለማስታወቅ እና ታክስ ባለመክፈል የሚጣል ቅጣት የዘገየውን ጊዜ መሠረት በማድረግ ተለያይቶ መወሰን አለበት::

2/ ታክስ ከፋይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ወደ ገቢዎች ቢሮ የባንክ ሒሳብ ገቢ ያደረገ ቢሆንም የታክስ ማስታወቂያ በወቅቱ ሳያቀርብ ያዘገየ ከሆነ ቅጣት የሚጣልበት በአዋጁ አንቀጽ 103 ድንጋጌ መሰረት የታክስ ማስታወቂያ ባለማቅረብ ወይም ዘግይቶ በማቅረብ ብቻ ይሆናል::

13.. ታክስ ከተወሰነ በኋላ ባልተከፈለው ታክስ ላይ የሚወሰን ቅጣት

1/ አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ በተሰጠው በ30 ቀን ውስጥ ከከፈለ በአዋጁ አንቀጽ 37/ ንዑስ አንቀጽ 8 በተደነገገው መሠረት ወለድ የማይታሰብበት ሲሆን በተመሳሳይ የአስተዳደራዊ ቅጣትም ተፈጻሚ አይደረግበትም::

2/ ታክስ ከፋዩ በቅሬታ እና በይግባኝ ጊዜ ባልተከፈለ ታክስ ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል::ይህ ተፈጻሚ ሚሆነው በቅሬታ እና በይግባኝ ውሳኔ መሰረት በግብር ከፋዩ ላይ በሚጸናው የግብር መጠን ልክ ይሆናል::

14. መረጃ ያለመስጠት የሚያስከትለው ቅጣት

ማናቸውም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ገቢዎች ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 65 መሰረት በጽሑፍ ማስታወቂያ ሲጠይቀው በጽሁፍ በማስታወቂያው በተጠቀሰው ቦታ እና ጊዜ የተጠየቀውን መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መሥርያ ቤት የበላይ ኃላፊ በአዋጁ አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 7 በተደነገገው መሠረት 5000 ብር ቅጣት ይጣልበታል::

15. ስለቅጣት አወሳሰን

1/ ገቢዎች ቢሮ የሚወስነው አስተዳደራዊ ቅጣት የታክስ ውሳኔ በመስጠት የሚፈጸም ይሆናል::

2/ አንድ ድርጊት መፈጸም ወይም ያለመፈጸም የሚያስከትለው ቅጣት በአንድ ታክስ ብቻ ያልተወሰነ ሲሆን እያንዳንዱ ቅጣት ለየብቻው ከተወሰነ በኋላ ሁሉም ቅጣቶች ተጠቃለው ይጣላሉ::ይህም ተፈፃሚ የሚሆነው በተለያዩ የታክስ ዓይነቶች ለሚፈጸሙ የሚከተሉት ጥፋቶች ብቻ ነው::

ሀ. ሰነድ ባለመያዝ፣

ለ. ታክስ በጊዜው ባለማስታወቅ፣

ሐ. ታክስ ዘግይቶ መክፈል፣

መ. ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ፣

ሠ. ታክስ መሸሽ

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ የተሻሩ አዋጆች ተፈጻሚ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንም::

2/ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሂደት ውሳኔ ሳያገኙ የቆዩ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ::

17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያዉ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በክልሉ ገንዘብ ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል::

ባህር ዳር

መስከረም 18 ቀን 2012 ዓ.ም

ጥላሁን መሀሪ አንተነህ (ዶ/ር)

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር

ቢሮ ኃላፊ